# አንበሳው የኢትጵያ ልጅ፤

ከኣላማው ኣማረ (ካናዳ)

ሞት ያማረው ጂሃድስት ሂወቱን የጠላ
ጦርነት ሊያካሂድ በሻዕብያ ከለላ
ከታሪክ የማይማር ደንቆሮ ቱልቱላ
የኢሳያስ ኣሽከር የዘመኑ ኣተላ
 በጫረው ጦረነት ባዶዋ ተቆላ።
ቢነግሩት ኣይሰማ ቢመከር ቢለመን
ነገር የማይገባው በሰለጠነው ዘመን
ልቡ ተወጥሮ በኣጉል ጀብደኝነት
ሶፍክር ከረመ ሊግጥም ጦርነት
ራሱ  በፈጠረው ባመጣው ጣጣ
ሜዳ ላ ቀረ በጀግኖች ቆረጣ
ለማይቀር ሽሽት ለማይቀር ፍርጠጣ
ዝም ከማለት ምነው ኣቅል ኣጣ
ትእግስት እንደ ፍርሃት ተቆጥሮ
ያ ሁሉ ቀረርቶ ያ ሁሉ እሮሮ
ሳምንት የማይሰነብት ኣጉል ጉራ
ራሱን ክቦ እንደ ተራራ
ባዶ ጩሀት ቁምነገር ኣልባ
ከመሞቃዲሾ የሮጠ ኪሰማዮ ገባ።
ሞት ያማረው ኣህያ ቀኑ የደረሰ
ኣንበሳ ከተኛበት ህዶ ቀሰቀሰ
እንኳንስ እንደዛሬ ታንክ ኣስከትሎ ሰነቁን ይዞ
ድል ማድረግ ልማዱ ነው በእግርም ተጉዞ
ኣለም ተገረመች ምላዋን ዋጠች
ማንስ ይናገር ማንስ ይተች
 ሲወደስ ከርሞ እየተባለ ጅግና
ብቅ ብሎ ጠፋ እንደ ደመና
ሳምንት የማይቆይ የማይድን ከፍርጠጣ
ኢሳያሰ ኣፈወረቂ ባመጣበት ጣጣ
ማሩኝ እያለ በህፍረት ተቀጣ
እንግዲህ ምን ይሆን የሻዕብያስ እጣ?
ጥንትም ቢሆን ኣለማወቅ ነው እንጂ
ተሸንፎ ኣያውቅም የኢትዮጵያ ልጅ
ለወዳጁ ማር ነው ለጠላቱ ኮሶ
ጦርነትም ያውቃል ኣይስትም ተኩሶ
የኢትዮጵያውያን ጀግንነት የታወቀ ነው ባለም
የሰው ኣይፍልግም  የራሱንም ኣይሰጥም
ሂወቱን ይሰዋል ላገሪቱ ጥቅም

ኣትንኩኝ ባይ ነው ከጥንት ጀምሮ
ከመጡበትም እግራቸውን ሰባብሮ
ይመልሳቸዋል ሽንፈትን ኣስተምሮ።

ይዘፈንለት ለዛ ጀግና ሰራዊት
የድል ኣርበኛ ውለታውን የማይስት
ድል ኣድራጊ በየሄደበት ቦታ
የኢትዮጵያውነት ኣርማ የህዝቧ ኣለኝታ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ኮርታ ትኖራለች።